

# መልካም ዘመን!










ምኞቴን ላቅርብ፣
ሰላምታየን ጭምር፣
ለታላቁ ሕዝብ፣
በያለበት ምድር።
በውቢቷም ሀገር፣

አቻምናን አናስብ፣
ጥሎ የሄደውን፣
ዳግም ይምጣ ይዝነብ፣
ይውሰድ የቀረውን።

ተከዜ አሻቅቦ፣
መንገዱ ነው ሰዎች፣
እሱም ሄደ ጠግቦ፣
አለወርድ ብሎ ታች።

አይ በሽሎ፣ ገራዶ፣
ወረዱ ወደታች፣
አባይ ጮኸ ወርዶ፣
ሀገር በቃኝ አለች!
መንገዱ ተንዶ፣
አይመለስ ሂዶ።

የወጣው ይከማች!
ኢትዮጵያ ትድመቅ፣
ብዙ ተሸከመች፣
ያ ይብቃ ይለቅ፣
ይግቡ የሷ ልጆች።

እናንተን ያሰንብት፣
ኢትዮጵያን ይጠብቅ፣
ያለሷ አይሆንም፣
አፍሪቃም አትደምቅ፣
ያለኢትዮጵያ
አይጠፋም ይህ ዓለም?

ሕዝብማ አይሰርቅም፣
ተሰረቀ ይባል፣

ወርቁ ባይገኝም፣
ሌባችን ተይዟል።

ሃምሳ ሺ ኩንታል፣
ጠፋ ከመካዝን፣
አወል በረካ ሲል፣
ያዙት የጠጣውን፣
ከመርካቶ መሀል!

እሱን ግን ሰቀሉት፣
ታሞ ነበር ሊሞት፣
ቶሎ ገላገሉት፣
ታሪክ ሰራ ድንገት፣
ታወቆ በሌብነት፣
ዓለም ፈረደበት።

ፈረንጅ ጥበበኛ
አውቀዋል እንወቅ፣
ምን አሉ ስለኛ፣
የራበው ሲሳለቅ፣
በደስታ፣ በሀዘን
የበላው ሲደለቅ፣
አይ ሰው! አይ ወገን፣
ሲጠሉት የሚንቅ።

ያኑር ያክርማችሁ፣
ታሪክ ናችሁ ቅርሶች፣
ይቆይ ትውልዳችሁ፣
የኢትዮጵያ ሕዝቦች።

ይመስክር ገጻችሁ፣
አበባዎች ናችሁ።

አጥሩ ይውጣ ከላይ፣
ክልል አይለያችሁ፣
ይጥፋ የሱ ራዕይ፣
እናንተ አላችሁ፣
የኢትዮጵያ ናችሁ።









**እጅግ ታምራላችሁ፣**
**አምላክ ሲፈጥራችሁ!**